**ማስጠንቀቅያ ፡ እሳተ-ጎመራ**

**እውነታዎች**: በዋሽንግተን ክፍለሃገር እሳተ ጎመራ ፈንድቷል። ይህ የእሳተ-ጎመራ ኣደጋ፡ ሃይለኛ ግለት ያለቻውን ኣመድ፡ ዓለቶች፡ ፈሳሾች፡ ጭቃና የመሬት ፍርስራሽ መትፋትን ያጠቃልላል። የእሳተ ጎመራው ፍንዳታ በመንገዶች፡ በመብራትና ውሃ ኣገልግሎቶች፡ በንብረት ላይ ጉዳት ሊያስከትልና ነፋስና ደመና ከቦታ ወደ ቦታ በሚንቀሳቀሱበት ግዜ ያንን የእሳተ ጎመራ ኣመድ ይዘው ስለሚጓዙ ብዙ መቶ ማይልስ ርቀው ለሚገኙ ሰዎች ሳይቀር ለጤና ኣስጊ የሆነ ሁኔታ ለፈጠር ይችላል።

**ምን ማድረግ ያስፈልጋል:**

- ከቤትዎ እንዳይወጡ ወይም ደግሞ ጭራሹን ቤትዎን ለቀው እንዲወጡ ሊታዘዙ ስለሚችሉ፡ ለዚሁ ራስዎን ማዘጋጀት።
- በቤትዎ ውስጥ እንዲቆዩ ከተጠየቁ፡ በቤት ውስጥ ለመቆየት ተዘጋጁ። ቤተሰቦችዎንና ያሎትን ለማዳ እንስሳዎችን በቤት ውስጥ ኣስገቡ። በሮችን፡ መስኮቶችን እንዲሁም የእሳት ማንደጃ በሮችን ይዝጉ፡ በየደጃፉና በማናቸውም ንፋስ ሊያስገቡ በሚችሉ በሮች ስር እርጥብ ፎጣዎችን ያኑሩ።
- ከውጭ ኣየር የሚስብ ማቀዝቀዣም ሆነ ማሞቅያ ኣጥፉ።
- በእርስዎና በውጭ ባለው ኣየር መካከል ማናቸውም ግንኙነት ወይም ክፍተት እንዳይኖር ለማድረግ፡ በእጅዎ ባለ የሆነ ማፈኛ የውጭ ኣየር ሊያስገቡ የሚችሉ ቀዳዳዎችን ለመዝጋት ተዘጋጁ።
- ሊከተል ከሚችል ጉዳት ሳንባዎን ለመከላከል ፊትዎን በማስክ ይሸፍኑ። የመተንፈስ ችግር ካለቦት የኣዝማ መከላከያ ዕቅድን ተከታተሉ ።
- ዓይኖችዎን ከኣደጋ ጠብቁ። ዓይን ውስጥ የሚሰኩ ሌንስ የሚያደርጉ ከሆነ እሱን ኣውጥተው፡ የዓይን መነጽር ወይም የዓይን መከላከያ መንጽር ያድርጉ።
- ቦታዎን እንዲለቁ ከታዘዙ ወድያውኑ ቦታዎን ይልቀቁ። በቦታ መልቀቅያ ማስታወቅያ ላይ የሰፈሩትን መንገዶች ብቻ ተከተሉ። ኣንዳንድ መንገዶች ምልክቶችና ጽሁፎች ሊደረግባቸው ይችላል።
- ኣደጋውን በሚመለከት ኣዲስ መረጃ እንዳለ ለማወቅ በቀጣይነት ሬድዮ ተከታተሉ ።
- ***ይህንን መልእክት ለመረዳት፡ ለማየትም ሆነ ለመስማት የማይችል የሚያውቁት ሰው ካለ፡ እባክዎትን መልእክቱን ኣስረዷቸው።***

**ጠቃሚ ዌብሳይቶች:**

http://www.seattle.gov/emergency-management/what-if/hazards/volcano-hazards-including-lahars

http://mil.wa.gov/emergency-management-division/hazards/volcano

http://www.ready.gov/volcanoes